**AMHARIC A1 – STANDARD LEVEL – PAPER 2**
**AMHARIQUE A1 – NIVEAU MOYEN – ÉPREUVE 2**
**AMHARE A1 – NIVEL MEDIO – PRUEBA 2**

Wednesday 22 May 2002 (morning)
Mercredi 22 mai 2002 (matin)
Miércoles 22 de mayo de 2002 (mañana)

1 hour 30 minutes / 1 heure 30 minutes / 1 hora 30 minutos

INSTRUCTIONS TO CANDIDATES

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Answer one essay question only. You must base your answer on at least two of the Part 3 works you have studied. You may include in your answer a discussion of a Part 2 work of the same genre if relevant. Answers which are not based on a discussion of at least two Part 3 works, will not score high marks.

INSTRUCTIONS DESTINÉES AUX CANDIDATS

- Ne pas ouvrir cette épreuve avant d'y être autorisé.
- Traiter un seul sujet de composition. Vous devez baser votre réponse sur au moins deux des œuvres de la 3e partie que vous avez étudiées. Le cas échéant, vous pouvez inclure dans votre réponse une discussion sur une œuvre du même genre littéraire étudiée dans la 2e partie du programme. Les réponses qui ne sont pas basées sur au moins deux des œuvres de la 3e partie n'obtiendront pas une note élevée.

INSTRUCCIONES PARA LOS ALUMNOS

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Elija un tema de redacción. Su respuesta deberá basarse en al menos dos de las obras estudiadas en la Parte 3. Se podrán hacer comentarios sobre una obra de la Parte 2 del mismo género, si fuera necesario. Las respuestas que no incluyan una discusión sobre al menos dos obras de la Parte 3 no recibirán notas altas.

ከሚከተሉት በአንዱ ሐተታ ፃፍ (ፃፊ)። መልስህ(ሽ) በክፍል 3 ባጠናህቸው(ሻቸው) ሁለት ሥራዎች ላይ መመሥረት አለበት። በክፍል ሁለት ሥር ካለ አንድ ተመሳሳይ የስነጽሑፍ ዘር መጠነኛ ማጣቀሻ ማስገባት ይፈቀዳል። ይህ ግን በክፍል 3 ሥር ከሚገኙ ቢያንስ ሁለት ሥራዎች በተጨማሪነት ብቻ መሆን አለበት። ሌሎች ሥራዎችን ማጣቀስም ይቻላል። ሆኖም የመልስህ(ሽ) አቢይ ክፍል ሌሎቹ ሥራዎች ላይ መመሥረት የለበትም።

*ድራማ*

1. ተከታዩን

(ሀ) ተውኔት የተሟላ የሚሆነውና ሀይልም የሚያገኘው በመድረክ ሲከወን (ሲታይና ሲደመጥ) ነው። ይህንን ሀሳብ አስረዳ።

ወይም ቀጣዩን ምረጥ።

(ለ) ከልቦለድ በተለየ በተውኔት ስለገፀባህርያቱ ማንነት የምናውቅባቸውን መንገዶች ያነበብካቸውን ተውኔቶች ምሳሌ በማድረግ ግለጽ። ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ፀሐፊ ተውኔቶች የተጠቀሙባቸውን ተውኔታዊ አቀራረቦች በማነጻጸር ሀሳብህን አስረዳ።

*ረጅም ልቦለድ*

2. ተከታዩን

(ሀ) አንድ ገፀባህሪ መለያ ባህርያቱን ይዞ በልቦለድ ውስጥ ከተዋወቀ በኋላ ያለበቂ ምክንያት በባህርይው (በሰብእናው) ላይ ትልቅ ለውጥ ሊከሰት አይገባም። በዚህ ሀሳብ ምን ያህል ትስማማለህ? ካጠናህቸው ስራዎች መካከል ሁለቱን በማነፃፀር ሐሳብህን አስረዳ።

ወይም ቀጣዩን ምረጥ።

(ለ) የአንድ ልቦለድ የትረካ አቅጣጫና ታሪኩ የተነገረበት ሁኔታ ለልቦለዱ የሚኖረን ግንዛቤ ላይ ተጽእኖ ያሳድራል። በዚህ ሀሳብ ምን ያህል ትስማማለህ?

*ሥነግጥም*

3. ተከታዩን

(ሀ) ከሌሎች የስነጽሑፍ ዘርፎች ደራሲዎች በበለጠ ገጣሚው ጥሩ የቋንቋ ችሎታ ሊኖረው ይገባል። ስራዎቻቸውን ያነበብካቸው ሁለት ገጣምያን በአንባቢው ላይ ተጽእኖ ለማሳደር ቋንቋን እንደምን እንደተጠቀሙበት እያነፃፀርክ አሳይ።

ወይም ቀጣዩን ምረጥ።

(ለ) ግጥም ሐይሉ የሚታየው በጥልቀት ስሜትንና ሁኔታን ለማሳየት በመቻሉ ነው። ይህንን ሐሳብ መሠረት በማድረግ ያነበብካቸውን ገጣምያን ስራዎች አነፃፅር።

ስድ ንባብ (ከረጅምና ከአጭር ልቦለዶች ሌላ)

4. ተከታዩን

(ሀ) ከአጭር ልቦለድና ከረጅም ልቦለድ ውጭ ባነበብካቸው ስድ ጽሑፎች አማካኝነት ጸሐፊዎቹ አንባብያንን ለማሳመን ያደረጉት ጥረት ምን ይመስላል?

ወይም ተከታዩን ምረጥ።

(ለ) ከአጭር ልቦለድና ከረጅም ልቦለድ ውጭ ያሉ ስድ ጽሑፎች በማንበብህ ስለህይወት ያለህ ግንዛቤ ተለውጧል? ያነበብካቸውን ሁለት ወይም ሦስት ስራዎች ምሳሌ በማድረግ ፀሐፊዎቹ ግንዛቤህን ለመለወጥ ለምን እንደቻሉና ምንስ ያህል እንደተሳካላቸው አሳይ።

አጭር ልቦለድ

5. ተከታዩን

(ሀ) አጭር ልቦለድ ነጠላ ግብ ያለው ነው። ታሪኩም በጥድፊያ ይቀርባል። እነዚህን ሁለት የአጭር ልቦለድ ባህርያት ያነበብካቸውን ሁለት ወይም ሦስት አጭር ልቦለዶች በማነጻጸር ግለጽ።

ወይም ቀጣዩን ምረጥ።

(ለ) በአጭር ልቦለድ የገፀባህሪ ቀረጻ ትልቅ ስፍራ ይሰጠዋል። ካነበብካቸው አጭር ልቦለዶች መካከል በገፀባህርያት ቀረጻ ረገድ የተዋጣለት የትኛው ነው? ለምን?

ሁለገብ (አጠቃላይ)

6\. (ሀ) በማንኛውም የስነጽሁፍ ስራ ደራሲው በቀጥታ ስለገፀባህርያቱ ማንነት ሊናገር አይገባም። አንባቢው ታሪኩን ተረድቶ ስለገፀባህሪያቱ ሰብዕና የእራሱን ፍርድ መስጠት አለበት። በዚህ ሐሳብ ትስማማለህ? ለምን?

ወይም

(ለ) አንድ ደራሲ ከፍተኛ የምናብ ኃይል የሚያስፈልገው ሲሆን ይኸው ሐይል በተለያየ ሁኔታ ሊታይ ይችላል። በክፍል 3 ያነበብካቸውን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በመጥቀስ ደራሲዎቹ ከላይ የተጠቀሰውን ሐሳብ ትክክለኛነት ለመደገፍ ወይም ለመቃወም እንደሚያስችሉ በንጽጽር አሳይ።

ወይም

(ሐ) የስነጽሑፍ ስራ ህይወት ተስፋ የሞላባትና ብሩህ መሆኗን ብቻ ሳይሆን አሳዛኝ ገጽታዋንም ማቅረብ አለበት። በክፍል 3 ያነበብካቸውን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በማነጻጸር ይህንን ሐሳብ አስረዳ። እያንዳንዱ ስራ ይህንን መመዘኛ ማሟላቱንና እንደምን ማሟላት እንደቻለ ተመልከት።

ወይም

(መ) ደራሲዎች በመቼት አማካኝነት ገፀባህሪያቶቻቸውን ለአንባቢያን ያሳያሉ (ያስተዋውቃሉ)። የመቼትን አቀራረብና ተግባር በክፍል 3 ካጠናሀቸው ስራዎች መካከል ቢያንስ ሁለቱን በመጥቀስ አስረዳ።